የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.8
ADDIS ABABA 9th January, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፭/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለልማት ፖሊሲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……ገጽ ፲፪ሺ፹፮

## Content

Proclamation No.1165/2019

French Development Agency Credit Facility Agreement for Financing Development Policy Program Ratification Proclamation….....Page 12,086

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፭/፪ሺ፲፪

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለልማት ፖሊሲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፹፭ ሚሊዮን ዩሮ (ሰማኒያ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.ኤ.አ ጁን ፮ ቀን ፪ሺ፲፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1165/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE FRENCH DEVELOPMENT AGENCY**

**WHEREAS**, a Credit Facility Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the French Development Agency (AFD) stipulating that the French Development Agency shall provide to the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit Facility in an amount of Eighty Five Million Euros (EUR 85,000,000); for Financing Development Policy Program was signed in Addis Ababa on the 6th day of June 2019;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of November, 2019;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለልማት ፖሊሲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፭/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.ኤ.አ ጁን ፮ ቀን ፪ሺ፲፱ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር CET 1083 02 W ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፭ ሚሊዮን ዩሮ (ሰማኒያ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "French Development Agency Credit Facility Agreement for Financing Development Policy Program Ratification Proclamation No. 1165/2019".

**2. Ratification of the Agreement**

The Credit Facility Agreement No CET 1083 02 W signed in Addis Ababa on the 6th day of June 2019 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the French Development Agency is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of a Credit Facility in an amount of Eighty Five Million Euros (EUR 85,000,000); in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Facility Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 9th day of January, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**